# ኣቢይ ኣሕመድ ዓሊ፥ ኣስተዳደግ የበደለው ኣደገኛ ኣምባገነን

**(ዶር ብርሃነ ወልደሚካኤል 25/03/2026)**

ይህ ኣጭር ድርሰት በኣማርኛ የተጻፈው ስለኣገራቸው በሚያስቡ ኢትዮጵያውያን እንዲነበብ በማሰብ ነው።

ኣቢይ ኣሕመድ ዓሊ የተደበላለቀ ኣስተሳሰብ ያለው ሰው ነው። ይህ የኣስተሳሰብ ድብልቅ ከኣስተዳደግ የመነጨ መሆኑ ከመገመት በላይ ሆኖ ተገኝተዋል።

ኣሁን ማወቅ እንደተቻለው፡ ኣቢይ ኣሕመድ በመሸታ ቤት ያደገ፣ እውነተኛ ኣባቱ በእርግጥ ለማወቅ ያልቻለ እና ያልታደለ ሰው ነው። ኣሕመድ ዓሊ የተባሉ ሰው የእንጀራ አባት ዓይነት እንጂ በስጋ ግኑኝነት እንዳልነበራቸው መረጃ ወጥተዋል። በመሸታ ቤት ማደግ ራሱ የቻለ የኣኣምሮ ችግር የሚያስከትል ሁኔታ እንዳለው ኣያከራክርም። እንደዛ ሆኖም፡ ኣቢይ ኣሕመድ በተፈጥሮ የላቀ የጭንቅላት ብልህነት የታደለ ሰው ነው። ከእናቴ ተነገረኝ የሚለው የኢትዮጵያ ሰባተኛ ንጉስ ለመሆን በራሱ ውስጥ ገብቶበት ለመተግበሩ የእድሜ ልክ ጥረት እንዲያሳካ ኣድርጎታል።

የኢትዮጵያ ሰባተኛ ንጉስ ለመሆን ኣቢይ ኣሕመድ የተፈጥራዊ ብልህነቱ በመጠቀም ያደረገው የሚያስገርም ጥረት በብዙ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። ለኣብነት የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡

ሀ) በኢሃደግ ዘመን ወታደር ሆኖ በስልጣን የነበሩ ሃላፊዎች ትግርኛ ተናጋሪዎች ስለነበሩ የትግርኛ ቋንቋ ማወቅ ኣለብኝ ብሎ ጥሮ ከጥሩ በላይ የመናገር ችሎታ ኣዳብረዋል። የትግራኛ ቋንቋ ችሎታው እጅግም የሚደነቅ ነው።

ለ) ኣቢይ ኣህመድ ሲያድግ የኢስላም ሃይማኖት ተከታይ ሆኖ ነበር። የሚገርመው ነገር ግን፡ የእስላም ሃይየማኖት ተከታይ ሆኜ የኢትዮጵያ ንጉስ ለመሆን ኣልችልም ብሎ ኣስቦ ወታደር ሲገባ እንደ ክርስትያን ሆኖ ነው። ውትድርና መግባቱም ለንግስነት መድረሻ ዕላማ እንደሆነ መገመት ኣያዳግትም።

ሐ) ኣቢይ ኣሕመድ ከፋ ጠቅላይ ግዛት ተወልዶ ያደገ በመሆኑ ኦሮሞ ነው። ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ብዛት ያላቸው ብሔር ቢሆኑም ቁጥራቸው ለብቻው ወደ ስልጣን የሚያደርስ ኣይደልም። ስለዚህ ኣቢይ ኣህመድ የኣማራ ድጋፍ በማግኘት ነው ወደ ንግስነት ልመጣ የምችለው የሚል ግንዛቤ ኣስቀድሞ የደረሰበት ሃሳብ ነው። ለዚህ ሃሳብ ለማጠናክር ሲልም ኣንዲት ጎንደሬ የሆነች ሚስት ማግባት ጠቃሚ ሆኖ ነው ያገኘው።

መ) ኣቢይ ኣሕመድ የትምህርት ደረጃው ለማሳደግ ያደረገው ጥረት እጅግም የሚደነቅ ነው ምንም እንኳ በተለመደ መንገድ በመከተል ባይሆን። ከሰባተኛ ክፍል እንዴት ኣርጎ የዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚያክል ትምህርት የዶክተር መኣርግ ለማግኘት በቃ ብዙ ያነጋገረ ጉዳይ ነው። እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዉም ቢሆን የላቀ ጭንቅላት እንዳለው የሚያመለክት ነው።

ስለዚህ፣ ኣቢይ ኣሕመድ ተፈጥራዊ ችሎታ እንዳለው ግልጽ ቢሆንም ወደ ግላዊ የንግስነት ህልም ለመድረስ ብቻ የሚያውለው በመሆኑ ነው የሱ ችግር። ይሀን ካልን በኋላ፣ ኣቢይ ኣሕመድ እንዴት ዓይነት የላቀ የመታለያ ስልት ተጠቅሞ ወደ ስልጣን እንደመጣ ማያተ ተገቢ ነው።

በኢሃደግ ዘመነ-መንግስት ኣቢይ ኣሕመድ ከባዶ ተነስቶ ኣስከ ሚኒስተር ደረጃ ደርሶ ነበር። በኣንድ ወቅት ሃላፊዎቹ የነበሩ በስራው ስላልተደሰቱ፣ ወረኛ ሰው ሆኖም ስላገኙት፡ ኣባርረው ወደ ኦሮሞ ኣስተዳደር ነው የወረወሩት። የንግስነት ህልም ከኣቢይ ኣስተሳሰብ የማይለይ በመሆኑ ግን በኦሮሞ ኣስተዳደር ሳለ ኣንድ ለማ መገርሳ የሚባል ጅል የሆነ ሰው ኣግኝቶ መጫወቻ ኣደረገው። ኣቢይ አሕመድ የተጠቀመበት የመሰላል ስልት የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያ ወደ ስልጣን መምጣት ግዜው ኣሁን ነው የሚል ስነሃሰብ ነበር። የሃበሻ ብሔሮች ለሶስት ሺ ዓመት ሲገዙ ቆይተው ኣሁን ደግሞ ኦሮሞች ኣንደዛ ለሶስት ሺ ዓመት መግዛት ኣለባቸው ይሚል ሃሳብ ነበር። በዚህ ጥረት ለለማ መገርሳና ለሌሎች የኦሮሞ ልሂቃን በማሳመን ለግዝየውም ቢሆን እሱ ይያዘው ብለው ለቀውለታል። በኦሮሞ ህዝብ የገነፈለ ኣድማ የማይቀለበስ መሆኑ ተገንዝቦ የወቅቱ ጠቅላይ ምኒስተር ሃለማርያም ደሳለኝ ስልጣን ለኣቢይ ኣህመድ እንዲያስረክብ ተገደድ።

ከንግዲህ ወዲህ ኣቢይ የተረከበው ስልጣን ለማጠናከር ሲል፣ በኣንድ በኩል ፍቅር እና መደመር የሚባሉትን ኣሳቦች በማራመድ ኣብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፈጣሪ የተላከ መልእክተኛ እንደሆነ ኣርጎ ተቀበለው።  ነገር ግን፡ በዛ በዋዜማው ግዜም ቢሆን ኣቢይ ለስልጣን ያሰጉኛል የሚላቸው ሰዎች መግደል እና ማሰር ተያይዞት ነበር። ተታለው ወደስልጣን ያደረሱት ኣንደ ለማ መገርሳ ሳይቀሩ ኣደጋ ላይ ወድቀው በተለያየ ሁኔታ ከእገር ተባረው እንዲወጡ ተደረገ።

የኣቢይ ከፍተኛ የስልጣን ጥማት እንዴት የዕድሜ ልክ ጥረት ሆነ ይቀጥላል ወደሚል ስልት ተሻግሮ ኣሁን ኣገሪትዋ ወድቃበት ወደኣለችው የእርስ በርስ መፋጀት ደረጃ  እንድትደርስ ኣድርጎኣታል።

ከታሪክ የተማርነው ነገር ቢኖር፣ ኣምባገነኖች ስልጣን ላይ ተቆንጥጠው ለመኖር ማነኛውም ነገር ለማድረግ፣ ማለትም ህዝብ ቢያልቅ ኣገር ችግር ውስጥ ብትወድቅም፣ ደንታቸው ኣይደለም። ኣብይ ኣህመድ ደግሞ እንዲያውም የከፋ ኣምባገነን ነው። በትግራይ የፈጸመው ኣስከፊ ጀኖሳይድ፣ በኦሮሞና በኣማራ ክልሎች እየተካሄዳ ያለው የሰው እልቂት ለኣቢይ ደንታ የሚሰጡ ኣይደሉም። ኣሰብ የሚባለው ትረካም ቢሆን ለኣገር ይጠቅማል ብሎ በመቆርቆር ሳይሆን በኣንድ በኩል ህዝብ ይስብልኛል በማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለኤመሬቶች ጥቅም ሲል ይሚያደርገው ያለው የእብደት ዘመቻ ነው።

**ኣጽኖታዊ ማስጠንቀቅያ ለሚመለከታቸው ሁሉ**

ኣቢይ ኣሕመድ በቀላሉ ሊገመት የማይገባው በጣም ኣደገኛ ሰው ነው። ዓለም ሳይቀር ኣታሎ የኖቤል ሽልማት ያገኘ ሰው እኮነው። ኣደጋኛነቱ፣ የሌላ ኣገር ሰራዊት በማሳተፍ በገዛ ኣገሩ በፈጸመው ጀኖሳይድ እጅግም የከፋ ኣምባገነን ሰው መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በፈለገው መዋቅር መኖር መብቱ መሆኑ ሊታምንበት ይገባል።  በዚህ ኣኳያ ብቻ ነው የኢትዮጵያ ህዝቦች የእርስ በርስ መተባበር ሊያደርጉ የሚችሉ። ኣንድ ብሄር በሌሎች ብሄሮች የባላይነት ይዤ እገዛለሁ የሚል ኋላቀር ኣስተሳሰብ ለማስወገድ የሰላም ወዳጅ ሁሉ ጥረት ማድረግ ያስፈልገዋል። ይኽ ማለት የሰው ህይወት ዋስትና ቀዳሚነት መስጠት ስለሚገባ ነው። ስለዚህ ኣቢይ ኣህመድ የህዝብ ልዩነት በመጠቀም የስልጣን ኮረቻ ላይ ተንቋጦ ለመኖር ተጨማሪ ዕድል በምንም መልኩ መሰጠት የለበትም።

**ጥልቅ ኣስፈላጊነት ጸሎት ለፈጣሪ**

የፈጣሪ ስራ ስዉር ነው የሚባል ኣነጋገር ኣለ። ይህን በመካከለኛው ምስራቅ የሚካሄደው ያለው ጦርነት ምናልባትም ለዚህ ኣባባል እውን የሚያደርግ ሊሆን ይችላል። ኣቢይ ኣሕመድ የሚያደርጋቸው ድንፋታዎች ለኤመሬቱ ቢን ዛይድ ተማምኖ እንደሆነ ብዙ ማስረጃዎች ኣሉ። ሆኖም፣ ኢመሬት የኢስራኤል እና የኣመሪካ ጥገኛ በመሆንዋ ከኢራን በዘነበው ሚሳይሎች የራስዋ የመኖር እጣ ፈንታም ኣስጊ ሆኖባታል። ስለዚህ ይኸ የፈጣሪ ስዉር ስራ ሆኖ በኢትዮጵያ የህዝብ የእርስ በርስ መተላለቅ ሳያስከትል ኣገሪትዋ ከኣንባ ገነኑ ኣቢይ ኣሕመድ እንድትገላገል ፈቃዱ ኣንዲሆን መጸለይ ያስፈልጋል።

ተፈጸመ።